# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ትምህርት ቢሮ

## የ6ኛ ክፍል 1ኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና

## አማርኛ, ሰኔ 2016ዓ.ም/ JUNE 2024G.C

የጥያቄ ብዛት: 40 የተፈቀደው ሰዐት: - 1 ሰዐት

**አጠቃላይ ትዕዛዝ**

ይህ የአማርኛ ቋንቋ ፈተና ነው፡፡ በዚህ ፈተና ውስጥ 40 ጥያቄዎች ተካተዋል፤ ለእያንዳንዱ ጥያቄ ትክክለኛ መልስ የሆነውን አማራጭ የያዘውን ፊደል በመመረጥ ለመልስ መስጫ በተሰጠው ወረቀት ላይ በማጥቆር መልስ ይሰጣል፡፡ በፈተና ላይ የተሰጡትን ትእዛዞች በጥንቃቄ በማንበብ ፈተናውን መስራት ይጠበቅባችኋል፡፡ መልስ የሚሰጠው የመልስ መስጫ ወረቀት ላይ ነው ፤በመልስ መስጫው ሊይ ትክክለኛውን መልስ የሚጠቆረው በእርሳስ ብቻ ነው፤ ትክክለኛውን መልስ በማጥቆር ሲሰራ ለማጥቆር የተፈቀደው ቦታ በሙሉ በሚታይ መልኩ በደንብ መጥቆር አለበት፤ የጠቆረውን መልስ ለመቀየር ቢፈለግ በፊት የጠቆረውን በደንብ በማጥፋት መጽዳት አለበት፡፡ ለምሳሌ የጥያቄው መልስ የተመረጠው "ሐ" ቢሆን ከዚህ በታች ባለው መልኩ መልስ መስጠት አለበት

ሀ ለ ሐ መ

○ ○ ● ○

ፈተናውን ሰረቶ ለመጨርስ የተፈቀደው ሰአት 1 ሰአት ነው፡፡ ሰዐት ሲያበቃ የምንጠቀምበትን የመጻፊያ እርሳስ ማስቀመጥ እና ፈተናው መስራት ማቆም አለብን፡፡ ፈተናው እንዴት እንደሚሰበሰብ በፈታኙ/ኟ እስከሚነገር ድረስ በቦታችን ተቀምጠን መጠበቅ አለብን፡፡

መኮረጅ ወይም በፈተና ሰዐት የፈተናን ህግ የማያከብር ተፈታኝ ፈተናው አይያዝለትም፤ ፈተናውን እንዳይፈተንም ይደረጋል፡፡

ፈተናውን መስራት ከመጀመራቹሁ በፊት በመልስ መስጫው ላይ መሞላት የሚገባውን መረጃ ሁሉ በጥንቃቄ መሙላት አለባችሁ፡፡

**ፈተናውን መስራት ጀምሩ ሳይባል መጀመር አይፈቀድም !**

LIVEWORKSHEETS

መመሪያ አንድ ፡- ከ 1-10 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጭ መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ መስጫው ላይ አጥቁር/ሪ።

1. "ጽሞና" ለሚለው ቃል በፍቺ የሚመሳሰለው የቱ ነው?

   ሀ.ጥንቃቄ ሐ.ተመሰበ

   ለ.እልህ መ.ሀዋቃ

2. ተማሪዎቹ በህብረት ለማጥናት ቆረጡ። ለተሰመረበት ቃል አውዳዊ ፍቺ የቱ ነው?

   ሀ.አሰቡ ሐ.መከሩ

   ለ.ወሰኑ መ.አቀዱ

3. "በኢትዮጵያም " የሚለው ቃል በመነጣጠል እንዴት ይነበባል?

   ሀ.በ-ኢትዮጵያ-ም ሐ.በ-ኢትዮጵያም

   ለ.በኢትዮጵያ-ም መ.በ-ኢትዮ-ጵያ-ም

4. "ውጤት-አማ-ነት-ም" የሚለው ቃል በመገጣጠም እንዴት ይነበባል?

   ሀውጤታምነት ሐ.ውጤትነትም

   ለ.ውጤትነትም መ.ውጤታማነትም

5. "ደራ" ለሚለው በፍቺ ተቃራኒው ቃል_____ ነው።

   ሀ.ቀዘቀዘ ሐ.ሞቀ

   ለ.ደመቀ መ.ደረጀ



LIVEWORKSHEETS

6. መሬቱ ስለታረሰ ጥሩ ምርት ሰጠ። የተሰመረበት ቃል ምን አይነት ፍቺ ይዟል?

ሀ.ፍካሬያዊ ሐ.እማሬያዊ

ለ.ስውር መ.ድርብ

7. "ዓይን" ለሚለው ቃል ፍካሬያዊ ፍቺው _____ ነው።

ሀ.ማየ ሐ.የሰውነት አካል

ለ.ዋና መ.መለያ

8. ልጁ ልብስ የለውም፤ ቁሉ ይረሳል።"ልብስ" የሚለው ቃል በዚህ አረፍተ ነገር ውስጥ እንዴት ይነበባል?

ሀ.በዜማ ሐ.በመነጣጠል

ለ.ላልቶ መ.ጠብቆ

9. "የህጻናትን" የሚለው ቃል በምዕላድ እንዴት ተከፋፍሎ ይጻፋል?

ሀ.የህጻናት-ን ሐ.የ-ህጻናትን

ለ.የ-ህጻን-አት-ን መ.የ-ህጻናት-ን

10. በየቤታችን ሄድን።"በየቤታችን" የሚለው ቃል ነጻ ምዕላዱ የቱ ነው?

ሀ.ቤት ሐ.በቤት

ለ.የቤት መ.ቤታ



LIVEWORKSHEETS

መመሪያ ሁለት፡- ከ11-16 ላሉት ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች በመምረጥ በመልስ መስጫ ላይ በማጥቆር መልስ/ሽ፡፡

ምንባብ አንድ

ለበጎ ስሜትም ሆነ ለጨለምተኛ ስሜት መነሻ ምክንያቱ የታሰበ ሀሳብ ነው፡፡ ሀሳብ የህይወትን ፈተናዎች ለመሻገርና ራስንም ሆነ ሌሎችን በብቃት ለመምራት ያስችላል፤ በሌላ በኩል አንድ ሰው ተሽመድምዶ እንዲቀር ምክንያቱ የገባ ሀሳቡ ነው፡፡ ስለዚህ ሀሳብና አስተሳሰብ የማንነት የዕጣ ፈንታ መሰረት ነው ማለት ይቻላል፡፡

የሰው ልጅ በጎ ሀሳብና ስሜት እንዲስማማው ሆኖ የተፈጠረ ነው፡፡ በጎ ሀሳብ በሚያስብበት ወቅት በጎ ስሜት ይሰማዋል፤ አእምሮውም በጤናማና ሰላማዊ ሁኔታ ይሰራል፡፡ በዚህ መሰረት ተቀባይነት ያለው በጎ ሀሳብ ብሩህ ተስፋና ተነሳሽነት እንዲፈጠር ያድርጋል፤ ወደ ስኬትም ያደርሳል፡፡

በሌላ በኩል የተዛባና አሉታዊ ሀሳብ አሉታዊ ስሜት መፈጠር ምክንያት ነው፡፡ አሉታዊ ሀሳብ አሉታዊ ስሜት እንዲፈጠር በማድረግ የአእምሮ ሰላምን ይነሳል፡፡ ስብዕናን ያዛባል፤ ከስኬት ይልቅ ወደ አስከፊ ህይወት ውስጥ ለመኖር ምክንያት ይሆናል፡፡

ምንጭ (ሥነ አዕምሮ፣ ገጽ 14፣2007 ዓ.ም)

11. ለዚህ ምንባብ ተስማሚው ርዕስ የቱ ነው?

ሀ.አሉታዊ ስሜት

ለ.አሉታዊ ሀሳብ

ሐ.የሀሳብ ጉልበት

መ.የሀሰብ መዘዝ

12. አእምሮን በጤናማና ሰላማዊ ሁኔታ እንዲሰራ የሚያደርገው ምንድን ነው?

ሀ.የተመጣጠነ ምግብ

ለ.አለመጨናነቅ

ሐ.ስራ መስራት

መ.በጎ ማሰብ



LIVEWORKSHEETS

13. ስብዕናን የሚያብበው ምንድን ነው?

ሀ.ህመም

ለ.አሉታዊ ሀሳብ

ሐ.በጎ ሀሳብ

መ.በሃሪት

14. የምንባቡ ዋና መልዕክት ምንድን ነው?

ሀ.የሰው ልጅ የሀሳቡ ውጤት መሆኑን ማሳየት

ለ.የሰው ልጅ ሀቀኛ እንዲሆን ማድረግ

ሐ.የሰው ልጅ በርትቶ እንዲሰራማድረግ

መ. የሰው ልጅ ተነሳሺ እንዲሆን ምድረግ

15. "ጨለምተኛ ስሜት " ለሚለው ቃል አውዳዊ ፍቺ_____ ነው።

ሀ.ተስፋ ሰጪ

ለ.ብርሀ ተስፋ

ሐ.ደስተኛ ስሜት

መ.ተስፋ አስቆራጭ

16. "ስኬት" ለሚለው ቃል በፍቺ የሚመሳሰለው የቱ ነው?

ሀ.ውድቀት

ለ.ደስተኛ

ሐ.ውጤት

መ.እድገት



LIVEWORKSHEETS

መመሪያ ሶስት ፡- 17-36 ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል በመምረጥ መልስ መስጫው ላይ አጥቁር/ሪ።

17."ወጣት አጥፊ የሚባሉት እድሜያቸው እስከ 18 የሚደርሱት ናቸው። እነዚህ ወጣቶች በእዚህ የእድሜ ደረጃ ክፉ ደጉን ለይተዋል ብሎ መናገር ይቻላል። ስለዚህ የተለያዩ ወንጀሎችን እንደሚፈጽሙ እሙን ነው።"

ይህ አንቀጽ በየትኛው የድርሰት አይነት ውስጥ ይመደባል?

ሀ.በአመዛዛኝ

ሐ.በገላጭ

ለ.በተራኪ

መ.ስዕላዊ

18. "ምንም አይነት የግዕዝ እውቀት የሌለው አንድ ጀማሪ ተማሪ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ቅኔ ቤት ሲገባ መጀመሪያ የግዕዝን ቋንቋ ወይም የግዕዝ ቃላትና ሰዋስው ማጥናት አለብህ አይባለም፡፡ምክንያቱም ግዕዝ ሳይሆን ቅኔ ለመማር ነውና የመጣው፡፡"

ይህ አንቀጽ በየትኛው የድርሰት አይነት ውስጥ ይመደባል?

ሀ.በገላጭ

ሐ.በአከራካሪ

ለ.በተራኪ

መ.ስዕላዊ

19. ጫት ________ አልኮልና ሲጋራ የአዕምሮ ስርዓትን ያዛባል። በክፍት ቦታው የሚገባው የስርዓተ ነጥብ አይነት የቱ ነው?

ሀ.፡

ሐ./

ለ.፤

መ.፣

20. በርትቶ አጠና________በፈተና ጥሩ ውጤት አመጣ። በክፍት ቦታው የሚገባው የስርዓተ ነጥብ አይነት የቱ ነው?

ሀ.፡

ሐ.፣

ለ.፤

መ.!



LIVEWORKSHEETS

21. "ዶክተር" የሚለው ቃል በአህጽሮተ ቃል ሲጻፍ ______ ይሆናል።

ሀ.ዶክ/ር

ሐ.ዶክ/ር

ለ.ዶክ/ተር

መ.ዶ/ር

22. ሰውየው ገበዝ ______ ጥሩ ምርት አገኘ። በክፍት ቦታው የሚገባው አያያዥ ቃል የቱ ነው?

ሀ.ስለሆነ

ሐ.ከሆነ

ለ.እንደሆነ

መ.ቢሆን

23. የተሳከለትን ደብዳቤ ______ የደብዳቤውን መልስ ጻፈ። በክፍት ቦታው የሚገባው አያያዥ ቃል የቱ ነው?

ሀ.ከተቀበለ

ሐ.እንደተቀበለ

ለ.በተቀበለ

መ.የተቀበለ

24. በልቦለድ ውስጥ የሚገኘውን ታሪክ የሚላበስ የልቦለድ አላባ ምን ይባላል?

ሀ.መቼት

ሐ.ታሪክ

ለ.ገጸባህሪ

መ.ጭብጥ

25. በልቦለድ ውስጥ የሚተላለፈው መልዕክት የልቦለዱ ___ ይባላል።

ሀ.ጭብጥ

ሐ.ታሪክ

ለ.ግጭት

መ.መቼት



LIVEWORKSHEETS

26. ስለህይወት ታሪክ ጽሁፍ ትክክል ያልሆነው የቱ ነው?

ሀ.የባለታሪኩን የአስተዳደግ ሁኔታ ያካትታል፡፡

ለ.የባለታሪኩን የትውልድ ዘመን ይይዛል፡፡

ሐ.የስርአተ ነጥብ ህግን መከተል አያስፈልግም፡፡

መ.የአረፍተ ነገር አገነባብ ህግን ይከተላል፡፡

27. ከሚከተሉት ቃላት ውስጥ አንዱ የተጸኦ ስም ነው፡፡

ሀ.ውሻ

ለ.አንተ

ሐ.ክፉኛ

መ.ድሬዳዋ

28. የወል ስም የሆነው የቱ ነው?

ሀ.እኛ

ለ.ሰው

ሐ.ሳራ

መ.ረጅም

29. ጎበዙ ልጅ <u>ወዲያው</u> መጣ፡፡ የተሰመረበት ቃል____ ተውሳከ ግስ ነው፡፡

ሀ.የጊዜ

ለ.የቦታ

ሐ.የሁኔታ

መ.የመጠን

30. ሁለቱ ልጆች __________ያጠናሉ፡፡ በክፍት ቦታው የሚገባው የጊዜ ተውሳከ ግስ የቱ ነው?

ሀ.በፍጥነት

ለ.በዝግታ

ሐ.ዛፍ ስር

መ.ማታ ማታ



LIVEWORKSHEETS

31. "በየቤቱ" በሚለው ቃል ውስጥ ድህረ ግንድ ቅጥያ የቱ ነው?

ሀ.በ

ሐ.ቱ

ለ.ኡ

መ.የ

32. <u>አለምነሽ</u> በጊዜ ወደ ትምህርት ቤት ሄደች፡፡ የተሰመረበትን ስም የሚተካው ተውላጠ ስም የቱ ነው?

ሀእንተ

ሐ.እሷ

ለ.እንቺ

መ.እኔ

33. <u>ደግ</u> ሰው ወድቆ አይወድቅም፡፡ የተሰመረበት ቃል የ_____ ቅጽል ነው፡፡

ሀ.ባህሪ

ሐ.አይነት

ለ.መጠን

መ.ቁጥር

34. <u>ነጭ</u> ልብስ ቆሻሻ አይችልም፡፡ የተሰመረበት ቃል የ_____ ቅጽል ነው፡፡

ሀ.ባህሪ

ሐ.ቁጥር

ለ.መጠን

መ.አይነት

35. በተሻጋሪ ግስ የተመሰረተ አረፍተ ነገር የቱ ነው?

ሀ.ልጁ ተማሪ ነው፡፡

ሐ.ልጅቷ ሸጠች፡፡

ለ.ልጅቷ ሄደች፡፡

መ.ልጁ ቤት አለ፡፡

36. በማይሻገር ግስ የተመሰረተ አረፍተ ነገር የቱ ነው?

ሀ.ልጁ አነበበ፡፡

ሐ.ልጁ መዘገበ፡፡

ለ.ልጁ ሮጠ፡፡

መ.ልጁ ሰጠ፡፡



LIVEWORKSHEETS

መመሪያ ፡- 37- 40 ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት ትክክል የሆነውን መልስ ከተሰጡት አማራጮች በመምረጥ በመልስ መስጫ ላይ በማጥቆር መልስ/ሽ፡፡

ምንባብ ሁለት

አረ ተይ ዝንጀሮ ግፍ አትናገሪ
አሁን ትገኛለሽ አውድማ ስትጭሪ
አረ ተይ ዝንጀሮ ልቤን ቆርጠሺው
ለፍቼ ለፍቼ ሰብሌን ጨረስሺው
ዝንጀሮ ታረቀች ምላ ተማምላ
ማሽላውን ትታ ገብሱን ልትበላ
ዝንጀሮ መንጻሮ
በበላሽ ቀበሮ
ዝንጀሮ ከመጣ ሰብሉን ለመብላት
በወንጭፍ ገባሁት ተመለስ በሉት
ተይ ተመለሽ ዝንጀሮ ተንኮል ያጠፋሻል
ነፍስሽን በጤና ብትይዝ ይሻላል

37. ይህ ቃላዊ ግጥም የሚባለው መቼ ነው?

ሀ.በሰብል ጥበቃ ጊዜ
ሐ.በእርሻ ወቅት
ለ.በጉልጓሎ ጊዜ
መ.በአጨዳ ጊዜ

38. ዝንጀሮ ምን ብላ ነው ምላ የታረቀችው?

ሀ.ሰብሉን እንደማትበላ
ለ.ዳግመኛ ላለመምጣት ነው
ሐ.ማሽላውን ትታ ገብሱን ልትበላ
መ.ገብሱን ትታ ማሽላውን ልትበላ



LIVEWORKSHEETS

39. "ተንኮል ያጠፋሻል" ሲል -------- ለማለት ነው።

ሀ.ተንኮል ያኖርሻል

ሐ.ተንኮል ስሪ

ለ.ተንኮል ይጎዳሻል

መ.ተንኮል ያርቅሻል

40. "ግፍ" ለሚለው ቃል አገባባዊ ፍቺ የሚሆነው የቱ ነው?

ሀ.ስቃይ

ሐ.ሀሰት

ለ.እውነት

መ.ጡር

LIVEWORKSHEETS